**በቁጣህ አትቅሠፈኝ**

በቁጣህ አትቅሠፈኝ

በመዓትህ አትገሥጸኝ

የተገፋሁ ስደተኛ ነኝ

አዝ . . . . . . . .

መላው ሰውነቴ በኃጢአት ታማል

በደሌም እንደጎርፍ አጥለቅልቆኛል

ቀኑን በትካዜ በሙሉ ኀዘን

አሳልፌዋለሁ በማፍሰስ እንባን

አዝ . . . . . . .

ለሞት ተቃረብኩኝ ፈጽሞ ደከምኩ

ልቤ ተጨነቀ በስቃይም ጮኸኹ

ጌታ ሆይ አትርሳኝ ፈጥነህ አድነኝ

ከአንተ የሚሠወር ምንም አይኖረኝ

አዝ . . . . . .

ጠፋብኝ አጣሁት የዓይኔን ብርሃን

እንደ ድዳ ሆንኩኝ ተያዘ ልሳን

አምላክ ሆይ ወደ አንተ እጄን አነሣለሁ

በደሌን ዐውቄ በአንተ እታመናለሁ

አዝ . . . . . . . .

አንተ ከእኔ አትራቅ ንቀህ አትተወኝ

አምላክ ሆይ አሁኑ ፈጥነህ እንድትረዳኝ

ጭንቀቱ በዛብኝ አሳቤ በርትቶ

አልችልም መከራ ሆንኩ እንደ ባዘቶ

አዝ . . . . . . .

አንተ ይቅር በለኝ እኔ ስማጸንህ

በበደሌ ሳይሆን እንደቸርነትህ

ለጥቂት ጊዜ እንጂ የአንተ እንግዳ ነኝ

በዚህ ዓለም ስደት የምኖር ሰው ነኝ